በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
## ክፍል አምስት

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ግንቦት ፳፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

***በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን***

- ርዕሰ ጉዳያችንን አስመልክቶ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤ እነርሱም ስለ ነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ፥ የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም፤ በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእስያ ለክርስቶስ በኵራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ።›› ***ሮሜ 16፡3-5።*** እንዲሁም ‹‹በሎዶቅያ ላሉቱ ወንድሞችና ለንምፋን በቤቱም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልን።›› ***ቆላ 4፡15።*** በማለት የጻፈው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ተመዝግቦ ይገኛል።
- ስለዚህ ‹‹በቤታቸው ያለች ቤተ ክርስቲያን›› ማለት ምን ማለት ነው?
- በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በክርስትና እምነት ባመኑ አማንያን ቤት ሆና በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ለጸሎት የሚሰበሰቡባት ነበረች።
- የመጀመሪያይቱም ቤተ ክርስቲያን የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ነበረች። ‹‹ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ።›› ***የሐዋ 12፡12።***
- እንዲሁም ያመኑት በጵርስቅላና በአቂላ እንዲሁም በንምፋን እና በልድያ ቤት ይሰበሰቡ እንደነበር እናነባለን። ***የሐዋ 16፤ 18 እና ቆላ 4፡15።***

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

## *በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን*

- እነዚህን ጥቅሶች በዚህ መልክ ወስደን ካልተረጎምናቸው ጥቅሶቹን እንዴት በሕይወታችን ልንጠቀምባቸው እንችላለን?
- ወደ ቤቱ ስንገባ በውስጡ የሚገኙት፣ የሚያገለግሉትና የሚገለገሉበት እነማን እንደሆኑ በግድግዳው ላይ በሰቀሉአቸው ሥዕላት ለመለየት የሚያስችል እድል እናገኛለን፡፡
- ስፖርትን ወይም ሙዚቃን የሚያዘወትሩ ሰዎች በቤታቸው ግድግዳ በሰቀሉት ፎቶ ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ አድናቆታቸውም ለማን እንደሆነ ለመለየት እንደምንችለው ሁሉ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችም በቤታቸው ሃይማኖታቸው ምን እንደሆነ ያሳውቃሉ ወይም ያስረዳሉ፡፡
- እንደ ክርስቲያን በቤታችን የተሰቀሉት ምን ዓይነት ሥዕላትና ፎቶግራፎች ናቸው? በቤታችንስ ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች?
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥዕላት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ያላቸውን ጠቀሜታ በመገንዘብ ለቤት ማድመቂያነት ከማዋል ይልቅ ከፍተኛ ክብካቤ እንዲደረግላቸው ታላቅ ጥንቃቄ ታደርግላቸዋለች፡፡
    - *በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕላት ሰማያዊቱ ቤተ ክርስቲያን በምድር ከእኛ ጋር ያላትን አንድነት ያመለክታሉ፡፡ በሰማያዊቱ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የእግዚአብሔር ቅዱሳን በሥዕላቸው ተወክለው በምድር ባለችው ቤተ ክርስቲያን ይገኛሉና፡፡ የቅዱሳኑን፣ የመላእክቱን ሥዕል ስንመለከት ነፍሳችን በተመስጦ ሆና ከበጎነታቸው ትማራለች፣ በጸሎታቸውና በአማላጅነታቸውም እንዲረዱን ትጠይቃለች፡፡*

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

## *በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን*

- *ሥዕላት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ነጸብራቅ ናቸው። ቅዱሳን ሥዕላት የተማሩትም ያልተማሩትም በፊደል ቋንቋ ሳይሆን በቀላማት አስረጅነት መንፈሳዊውን ዓለምና ሕይወት ለመረዳት እንዲችሉ ያደርጋሉ።*
- *ሥዕላት በጥንቃቄ ከተሳሉ ታሪክን ወክለው ይገኛሉ። ይልቁኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥዕላት መንፋሳዊውንና ታሪካዊውን ገጽታ ቁልጭ አድርገው በቀላሉ የማሳየት ጉልበት አላቸው።*

- በቤታችን የሚገኙ ቅዱሳን ሥዕላት በቤተሰቡ አባላትና በሥዕላቱ በተገለጹት ቅዱሳን መካከል የተፈጠረውን አንድነት ከየትኛውም አስረጅ ነገር በላይ ማሳየት የሚችሉ ገላጮች ናቸው።
- በቅዱሳን ሥዕላት የተከበበች ቤተ ክርስቲያን በቤታችን አለችን? እነዚህ ሥዕላትስ ክርስትናችንን ብሎም ኦርቶዶክሳዊነታችንን መግለጽ ይቻላቸዋል?
- ለምሳሌ በመለኮታዊ ኃይሉ ሲገለጥ ማንም ሊያየው የማይቻለው የእግዚአብሔር አብ፣ የእግዚአብሔር ወልድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥዕል በቤታችን ይገኛል? ምስጢረ ቁርባን የተመሠረተበትና የተፈጸመበት የምሴተ ሐሙስ ሥዕልስ? *ማቴ 17፣ ማቴ 3፣ ማቴ 26።*
- *በመዝ 44፡9።* ‹‹በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።›› በማለት እንደተጻፈልን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታችን በቀኝ በኩል ሆና እንደታቀፈችው የምትታይበት ሥዕልስ በቤታችን አለን? በቤታችን በምንሰቅላቸው ሥዕላት ላይ ታላቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል።
- የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች! አሁን የትኞቹ ሥዕላት እንደሚገኙ ለመመልከት ወደ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ቤት በመግባት ቅኝት እናደርጋለን።

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

***በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን***

- ወደ ኦርቶዶክሳውያን ቤት ስንገባ ክፉ ሁሉ ወደ ቤቱ እንዳይቀርብ፣ ቤቱም ቤተ ክርስቲያን ሆና የጌታችን ፈቃዱ እንዲፈጸምባትና ደስ እንዲሰኝባት በመግቢያው ላይ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ሥዕል የቤቱ ጠባቂ ይሆን ዘንድ ተሰቅሎ ልንመለከት እንችላለን፡፡ *መዝ 33፡7-8፡፣ማቴ 18፡10፡፡*
- የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገባባትንና ከአመኑበት ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ጋር የሚኖርባትን ቤት የመግቢያ በር ይጠብቃታል፡፡

***በቤቱ መግቢያ ላይ***

- ‹‹እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።» *ማቴ 11፡28፡፡* በማለት እንደሚጣራ ሆኖ እጆቹን ዘርግቶ የተሰቀለውን የጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሥዕል ልናገኝ እንችላላን፡፡
- ይህም ሥዕል ወደዚህ ቤት የሚገቡትን ሁሉ ችግር፣ ሸክምና ፈተና በራሱ በማኖር ሰላምን ይሰጣቸው ዘንድ ይጋብዛቸዋል፡፡ *ገላ 3፡1፡፡*
- በተጨማሪም በዚሁ ቤት መግቢያ ላይ በስደቱ የግብጽና የኢትዮጵያን ሰዎች የባረከበትን የስደቱን ሥዕል ልናገኝ እንችላለን፡፡
- ይህን ሥዕል በቤታችን መግቢያ ላይ ማድረጋችን ጌታችን ከእመቤታችንና ከቅዱስ ዮሴፍ ጋር እንዲባርከን ያደርገናል፡፡ *ኢሳ 19፡25፣ ዕንባ 3፡7፡፡*
- እንግዲህ ይህን በማድረግ የጌታችን የአምላካችንን በረከት ከእናቱ ከእመቤታችንና ከቅዱሳኑ ጋር ወደምንቀበልበትና ሰላም ወደሞላበት ቤታችን እንግባ፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

***በማረፊያ ክፍል (Living Room)***

- *ጌታችን በተራራው ስብከት ሲያስተምር የሚያመለክተውን ሥዕል ልናደርግ እንችላለን፡፡ ማቴ 5 - 8፡፡*
- *ይህንም ሥዕል ስንመለከት የጌታችንን ቃሉን እያስታወስን (እያሰብን) ሰውነታችንንም እየተቆታጠርን ሕይወታችንንም የቃሉ ምስክርነት የሚሰጥበት ልናደርገው እንችላለን፡፡*
- *ይህን ቦታ ቤተሰቡ ሁሉ ከእንግዶቻቸው ጋር የሚሰባሰቡበትና ስለ አምላካችን ትእዛዛት የሚነጋገሩበት ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡*

***በማዕድ ቤት***

- *ጌታችን አምላካችን በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሕዝብ መግቦ ያትረፈረፈበት ሥዕል ሊኖር ይችላል፡፡ ማቴ 14፡14-22፡፡*
- *ይህን ሥዕል ስንመለከት ያለን ሀብትና የክፍፍሉ አለመመጣጠን ወይም ማነስ የማይገድበውን ሁሉን አትረፍርፎ የሚሰጠውን የጌታችንን በረከቱን (ስጦታውን) እናስተውላለን፡፡*
- *ወላጆች ጌታችን ሕዝቡን ከመመገቡ በፊት ስለዘላለማዊቱ መንግሥት ስለመንግስተ ሰማያት በማስተማር ከሥጋ ፍላጎታቸው በፊት መንፈሳዊውን ያሚላ መሆኑን ልብ ማለት ይገባቸዋል፡፡*
- *በዚህም መሠረት ለልጆቼ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን እያሚላሁላቸው ነው ወይስ ሐሳብ ብቻ የማመላልስ ነኝ? ብሎ ራስን መጠየቅም ያስፈልጋል፡፡*
- *ወላጆች ከቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች እያነበብን ያነበብነውንም ትርጉም ተምረን በመረዳት ለልጆቻችን እንደ ሥጋዊ ምግባቸው መንፈሳዊ ምግባቸውን እናዘጋጅላቸዋለን?*

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

- በማዕድ ቤታችን ከዚሁ በተጨማሪ የማርታና የማርያም ሥዕል ሊኖረን ይችላል፡፡ ሉቃስ 10፡38-42፡፡
- ይህን ሥዕል ስንመለከት ጌታችን ማርታን ‹‹ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።፡፡» ሉቃ 10፡41-42፡፡ በማለት የነገራትን ቃሉን እናስታውሳለን፡፡
- ወላጆችም ይህን አቀጣጫ በመከተል ማንኛውንም ነገር ከማድረጋቸው በፊት ማርያም እንዳደረገችው ከጌታችን እግር ሥር በመቀመጥ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግኑኙነት ማጥበቅና በጥልቅ መሠረት ላይ ማነጽ ይገባቸዋል፡፡
- ወላጆች በዚህ ዘመን ማርያምንም ማርታንም ሆነው መገኘታቸው እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

*በመመገቢያ ክፍላችን (Dinning Room)*

- ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የመመገቢያ ክፍላችንን በፍራፍሬዎችና በአበቦች ከማድመቅ ይልቅ ‹‹የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል፡፡›› ዮሐ 6፡57፡፡ ያለውንና የሕይወት እንጀራ የሆነውን ጌታችን አምላካችንን የምናስብበት የምሴተ ሐሙስ ሥዕል ብናደርግ መልካም ነው፡፡
- ይህን ሥዕል ስንመለከት ከቅዱስ ቁርባን መራቃችንን ልናስታውስ እንችላለን፡፡
- በተጨማሪም በሥዕሉ የሚገኘውን ይሁዳን ስንመለከት ኃጢአታችን ከቅዱስ ቁርባን ምን ያህል እንዳራቀንና ከቅዱሳንም አንድነት እንደለየን እናስተውላለን፡፡
- እየተመገብን ሥዕሉን መመልከታችን ልባችንም መንፈሳዊውን ምግብ እንዲመገብ ምክንያት ይሆነዋል

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

***የባለትዳሮች የመኝታ ክፍል***

- በቃና ዘገሊላ ተገኝቶ ጋብቻን የባረከ የጌታችን ሥዕል ሊኖር ይችላል፡፡ *ዮሐ 2፡1-11፡፡*
- የሥዕሉ መኖር ጌታችን ከእናቱ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሠርግ ቤቱ ተገኝቶ ጋብቻውን እንደባረከ በዚህም ቤት በመካከላቸው ተገኝቶ ሐሳባቸውን እንደባረከላቸውና በፍቅርም እንዳስተሳሰራቸው እንዲሰማቸው፣ እንዲረዱ እንዲያስተውሉ ይረዳል፡፡

***በልጆቻችን ክፍል***

- በልጆች ክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ ሚኪ ማውስን (Mickey Mouse) የመሳሰሉ የእንስሳትና የአዕዋፋት ሥዕሎች (ፎቶዎች) እናገኛለን፡፡
- የኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ቤት ግን ከልጆቹ አልጋ በላይ የሚጠብቋቸው መላእክት ሥዕል በሌላኛው በኩል በሚገኘው ግድግዳ ላይ ደግሞ ሕጻናትን የሚወዳቸውና ያቀፋቸው በሕጻናት የተከበበው የጌታችን ሥዕል ይኖራል፡፡ *ማቴ 19፡13-15፣ ማቴ 18፡1-10፡፡*
- በተጨማሪም በከብቶች ግርግም የተወለደው የጌታችንንና በሕጻንነቱ ሰማዕት የሆነው የቅዱስ ቂርቆስ ሥዕላት በልጆች ክፍል ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ *ማቴ 2፣ ዕብ 12፡1-3፡፡*
- ይህም ጎዳናቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ለጌታችን ለአምላካችንና ለቅዱሳኑም ቅርቦች ሆነው መንፈሳዊውን ዓለም በአግባቡ እየተረዱና መንፈሳዊነቱም እየተዋሃዳቸው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል፡፡
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! የኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ቤት በቅዱሳን ሥዕላት ብቻ ሳይሆን በተለያየ ቅርጽ በተሠሩ መስቀሎችም ጭምር የተባረከ ነው፡፡ *ገላ 6፡14፣ ፊል 3፡18-21፡፡*

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ - በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን

- ተፈጥሮን የሚያደንቁና የሚወዱም *በመዝ 91(92)፡12* ‹‹ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፥ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል፡፡›› እንደተባለው ወደ መንፈሳዊ ጎዳና ለማምራት የሚረዱአቸውን የዘንባባ… ሥዕላት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
- ዘንባባ ግንዱ ቢታይም ሥሩ ግን አይታይም፡፡ ለግንዱ ሕይወቱ ሥሩ ነው፡፡ በዚሁ ዛፍ ሥዕል አማካኝነት የማይታየው እግዚአብሔር የሚታየውን ሰው ከፍጥረታት ሁሉ አልቆ ሲመግበውና ሲያበረታው የሚኖር መሆኑን እንማርበታለን፡፡
- የዘንባባ ዛፍ ግንድ ውስጣዊ አካሉ ነጭ መሆኑ ‹‹ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፡፡›› *ሮሜ 12፡21፡፡* የተባለውንና በዚህም እየተመራ የሚኖረውን የጻድቁን ሰው የልብ ንጽሕና ያመለክተናል፡፡
- የዘንባባ ዛፍ ድንጋይ ሲወረውሩበት ወይም ሲያወዛውዙት ፍሬውን እንደሚያራግፍ ሁሉ ጻድቅ ሰውም ቅዱስ እስጢፋኖስ ‹‹ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡›› *የሐዋ 7፡60፡፡* በማለት እንዳደረገው ቅዱሳን በጭቃኔና በግፍ ለሚፈታተኑአቸው ሁሉ የሚጸልዩላቸው መሆኑን እንማርበታለን፡፡
- *በመዝ 18(19)፡1፡፡* ‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል፡፡›› በማለት መዝሙረኛው ዳዊት እንደዘመረው የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ለማሰብ ይረዳን ዘንድ የከዋክብትና የጨረቃም ሥዕላት በቤታችን ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
- የእግዚአብሔር ቤተሰቦች! የሰው ወገኖች በጎበኟችሁ ጊዜ ሁሉ በቤታችሁ የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን ሊያገኟት ሊመለከቷት ይችሉ ይሆን? ቤተሰቡ ሁሉ የሚጠቀምባቸውን መንፈሳውያን ሥዕላትስ ይመለከቱ ይሆን? … ይቆየን፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org